በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፐሊክ መንግስት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ፤ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ ክትትልና አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት 2005 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ራዕይ፤ ተልዕኮ፤ አላማ እና እሴቶች 2

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር........ 3

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር አደረጃጀት........ 4

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሠው ኃይል 4

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የፋይናንስ ምንጭ 4

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ገቢ 5

የኦዲቱ አላማ 5

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ /ሥልት/ 6

ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) 6

የኦዲቱ ጭብጦች (Audit Issue) 6

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ 7

የአሰራር ስርዓት መግለጫ........ 8

ክፍል ሁለት 9

የኦዲት ግኝቶች........ 9

ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ ምርቶች አያያዝና የመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታን በተመለከተ፣ 9

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፍቃድ የሰጠው ወይም ያሳተመው መሆኑን በተመለከተ፤ 14

በማዕከላት ከምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ መደረጉን በተመለከተ፤ 15

በማዕከላት ከምርት አሠባሰብ እስከ ሽያጭ ሂደትን የመከታተያ ስርዓትን በተመለከተ፤........ 16

የማረሚያ ቤቱን ምርት ለመሸጥ የማስተዋወቅ ስራን በተመለከተ፤........ 18

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ መመሪያ ማዘጋጀቱን እና ለሚመለከታቸው ማዕከላት ማሰራጨቱን በተመለከተ፤ 21

በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የውስጥ ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፤ 23

በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጻ ቅጾች መጠቀምን በተመለከተ፤........ 25

ሁሉም ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቶች አስተዳዳሪ ሪፖርት ማቅረባቸውን በተመለከተ፤........ 26

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የስርዐተ-ፆታ እና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጉዳይ በስራ እቅዱ ተካቶ (Mainstreaming) በሁሉም የስራ ሂደት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 26

ክፍል ሦስት........ 29

መደምደሚያ ሃሳቦች 29

ክፍል አራት........ 32

የማሻሻያ ሃሳቦች........ 32

አባሪ 1........ 35

አባሪ 2........ 38

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ማረሚያ ቤቶች ባሳለፉት አንድ ምዕተ አመት በይዘታቸውና በቅርጻቸው የተለያዩ ደረጃዎችን አልፈዋል፡፡ መደበኛ እስር ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሰረተው በ1916 ዓ.ም ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍኔሽን አባል ለመሆን ስታመለክትና ወንጀለኞች የሚታሰሩበት እስር ቤት እንኳን የሌላት ስለሆነ የማህበሩ አባል መሆን እንደማትችል ተቃውሞ ከገጠማት በኋላ ነው፡፡ በንጉሱ ጊዜ ወህኒ ቤት እየተባለ ይጠራ የነበረው ድርጅት በ1936 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 45/1936 ህጋዊ መሰረት ኖሮት፣ ተጠሪነቱ ለአገር ግዛት ሚኒስቴር ሆኖ፣ ስልጣንና ተግባሩ ተለይቶና የእስረኞች መብትና ግዴታ ታውቆ እንደገና ተደራጀ፡፡ ደርግ በ1966 ዓ.ም ስልጣን ከያዘ በኋላ የወህኒ ቤቱን የሰው ሀይል በወታደራዊና በፖሊስ አሰለጣጠን፣ አሰራርና ስርዓት በማጠናከር ጥፋተኛ የሚላቸውን ሰዎች የሚያስርበት እስር ቤት ሆኖ ቆይቷል፡፡
2. በ1983 ዓ.ም የደርግ ሥርዓት ከተለወጠ በኋላ በሀገራችን አዲስ ህገ መንግስት ወጥቶ ተግባራዊ በመሆኑ በህገ መንግስቱ መሰረት ፌደራላዊ የአደረጃጀት ስርዓት በመከተል ማረሚያ ቤቶች በፌደራል ደረጃና በየክልሎች እንዲዋቀሩ ተደርጓል፡፡ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ቀደም ሲል በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር ከዚያም ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በፍትህ ሚኒስቴር ስር በፌደራል ፖሊስና ማረሚያ ቤቶች ማስተባበሪያ ቢሮ ሲተዳደር ቆይቷል፡፡
3. ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ስር እንዲሆን የተደረገ ሲሆን በውስጡም ሁለት መምሪያዎች፣ አምስት አገልግሎት፣ አራት ማዕከላት ተደራጅቶ ከቆየ በኋላ በአዲሱ የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 365/95 መሰረት አደረጃጀቱ በኮሚሽን ደረጃ ሆኖ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት፣ የአዲስ አበባ አስተዳደር ማረሚያ ቤትና የድሬደዋ ካውንስል ማረሚያ ቤትን፣ የአደገኛ ቦዘኔዎች ተሀድሶ ማዕከል /Rehabilitation Center/ ያካተተ ተቋም ሆኖ ተደራጅቷል፡፡ የማረሚያ ቤቶችን አደረጃጀት በቀጣይነት ማሻሻል በማስፈለጉ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ መዋቅር ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ መሠረት በአምስት ዋና መምሪያዎች 26 መምሪያዎችና 13 አገልግሎቶች የአዲስ አበባ ዋና

መምሪያ የሸዋ ሮቢት፤ ዝዋይ፤ ቃሊቲና ድሬደዋ ማረሚያ ቤቶች መምሪያዎች ይዞ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ራዕይ፤ ተልዕኮ፤ አላማ እና እሴቶች

ራዕይ

4. መልካም አስተዳደር የሰፈነበት የህግ የበላይነት እና የታራሚዎች ሰብአዊ መብት የሚከበርበት የታረመና የታነጸ አምራችና ህግ አክባሪ ዜጋ የሚፈራበት ተቋም ሆኖ ማየት፤

ተልዕኮ

5. በፍርድ ቤት ውሣኔ ወደ ማረሚያ ቤት የሚመጡ የቀጠሮ እስረኞች/ታራሚዎችን በመቀበል የተጠናከረ የደህንነት ጥበቃ እና አስተዳደር፤ የመሠረታዊ ፍላጎት አገልግሎት ፤የተሃድሶ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት በማከናወን ታራሚዎችን ከአጥፊነት እና ወንጀለኛነት ባህሪ በማላቀቅ አምራች እና ህግ አክባሪ ዜጋ እንዲሆኑ በማድረግ ተቋሙ በወንጀል መከላከል እና የህዝብ ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ የበኩሉን ድርሻ መወጣት፤

ዓላማ

6. ታራሚዎችን ተቀብሎ መጠበቅ፤ ለታራሚዎች የተሐድሶ አገልግሎት በመስጠት የአስተሳሰብና የሥነ ምግባር ለውጥ እንዲያመጡ እንዲሁም ህግ አክባሪ ሠላማዊና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

እሴቶች፤

- የህግ የበላይነት ማክበር ማስከበር
- ፍታህዊነት
- ግልጽነትና ተጠያቂነት
- አሳታፊነት
- ሙስናን መጠየፍ፤
- በታማኝነትና በቅንነት ማገልገል፣
- ለለውጥ ዝግጁነት
- ሰብአዊ መብት ማክበር፤ አድሎ አለመፈጸም፤ አርአያነት ናቸው፡፡

<u>የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር</u>

7. ዋና ዋና ተግባራት፡-

- በፍርድ ቤቶች ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ መሠረት የሚላኩትን ታራሚዎች በመቀበል ይጠብቃል፣ ያርማል፣ እንዲሁም ከፍርድ ቤት የሚሰጡ ሌሎች ውሣኔዎችን ይፈጸማል፣
- ታራሚዎችን ፍርድ ቤት ያቀርባል፣
- ታራሚዎችን ጤንነት ይጠብቃል ፣ ነጻ ህክምና፣ ምግብና መጠለያ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ለታራሚዎች አካላዊና አዕምሮአዊ እንክብካቤ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ያከናውናል፣
- ታራሚዎች ከተለቀቁ በኋላ ራሣቸውን ለማስተዳደር የሚችሉና ለህግ ተገዥ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የቀለም ትምህርት፣ የሙያ ስልጠና፣ ማህበራዊ አገልግሎትና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
- በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ታራሚዎችን ከፌደራል ማረሚያ ቤቶች ወደ ክልል ማረሚያ ቤቶች ወይም ከአንድ ማረሚያ ቤት ወደ ሌላ ማረሚያ ቤቶች አጅቦ ያደርሣል፣
- ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የማረሚያ ቤቱን የሥነ ስርአት መመሪያ በመጣስ ለሚፈጽሙት ጥፋት ደንብና መመሪያ በሚያዘው መሠረት የሥነ ሥርዓት ቅጣቶችን ይወስናል፣ ይፈጽማል፣
- በሀገር አቀፍ ደረጃ ታራሚዎችን በሚመለከት መረጃዎችን እና ስታስቲኮችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣
- ታራሚዎች በሚያሳዩት የባህሪይ ለውጥ በህጉ መሠረት በአመክሮ እና በይቅርታ እንዲፈቱ ስልጣን ለተሰጠው አካል ሃሳብ ያቀርባል፣
- ኮሚሽኑን ለስራ አስፈላጊ የሆኑ የማረሚያ ጥበቃ አባላትን ይመለምላል፣ ይቀጥራል፣ ያሰለጥናል፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
- ኮሚሽኑ የሠራተኞችን የሙያ ብቃት ለማሳደግ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የስልጠና እድሎችን ያመቻቻል፣

- የታራሚዎችን አጠባበቅና አያያዝ ለማሻሻል የማረሚያ ጥበቃ አባላትና ሠራተኞችን ሙያ ብቃትና አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተመሣሣይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዱ ጥናቶችን ያከናውናል፤
- ለክልል ማረሚያ ቤቶች የሙያና የቴክኒክ እንዲሁም የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር አደረጃጀት

8. የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር አደረጃጀት በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሠው ኃይል

9. በፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል 2864 ሲሆን የሴት ጥበቃ አባላት 534 (12%)፤ የወንድ ጥበቃ አባላት 2986 (71%) ሲሆኑ የሴት የሲቪል ሠራተኞች 495 (11%) የወንድ የሲቪል ሠራተኞች ብዛት 147(3%) እና የኮንትራት ሠራተኛ ብዛት 12 በጠቅላላው 4174 ሠራተኞች ይገኛሉ፡፡

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የፋይናንስ ምንጭ

10. የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት የሚመደብ በጀት ሲሆን፣ በጀቱና ሥራ ላይ የዋለው እንደሚከተለው ተቀምጧል፡-

ዓ.ም	የተመደበ በጀት		ጠቅላላ የተመደበ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ				ሥራ ላይ የዋለ ጠቅላላ ወጪ	
	መደበኛ	ካፒታል		መደበኛ	በ%	ካፒታል	በ %	ሥራ ላይ የዋለ	በ %
2002	131,303,904	13,680,800	144, 984,704	123,432,044.62	94	2,425,803.59	17.7	125,857,848.25	86.8
2003	139,948,519.42	12,731,800	152,680,319.42	133,416,933.17	95	5,993,141.69	47	139,410,074.86	91.3
2004	214,415,368.72	192,421,300	406,846,668.72	204,618,345.39	95	184,223,880.10	96	388,842,225.49	95.5

ምንጭ፡- ከ2002፤ ከ2003 እና ከ2004 የኦዲት ሪፖርት የተገኘ፡፡

ማስታወሻ፡- በ2003 በጀት ዓመት ብር 4,236,306 ከካፒታል በጀት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተመላሽ/ በዝውውር/ ተደርጓል፡፡

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ገቢ

11. የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ከልማት ገቢ የሚሰበስብ ሲሆን፣ በ 2002 ዓ.ም ብር 6,035,628.38 (ስድስት ሚሊዮን መቶ ሰላሳ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሃያ ስምንት ከሰላሳ ስምንት ሳንቲም) ፣ በ 2003 ብር 5,885,148.11 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺ አንድ መቶ አርባ ስምንት ከአስራ አንድ ሳንቲም) እና በ 2004 ብር 7,300,032.98 (ሰባት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ከዘጠና ስምንት ሳንቲም ሲሆን በአጠቃላይ ብር 19,220,809.47 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሺ ስምንት መቶ ዘጠኝ ከአርባ ሰባት ሳንቲም) ገቢ ሰብስቦ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ገቢ አድርጓል፡፡

ስዕል 1: ከ2002-2004 የተሰበበሰ የውስጥ ገቢ



ምንጭ: የተሃድሶና ልማት ማእከላት ከ2000 እስከ 2004 በጀት ዓመት ከልማት ገቢ ሪፖርት የተወሰደ፡፡

የኦዲቱ አላማ

12. በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ፤ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ ክትትልና አፈጻጸም በቁጠባ፤ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ /ሥልት/

13. ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ 2002 እስከ 2005 ሩብ ዓመት ያለውን የምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብ፣ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ ክትትልና አፈጻጸምን የሚመለከት ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጲያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች /Ethiopian Performance Audit Standards/ መሰረት ነው፡፡ ለክዋኔ ኦዲቱ በተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶች መሠረት መረጃዎች ተሰብስበው ተተትነዋል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡

14. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በተኃድሶ ልማት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክቶሬት ሲሆን፣ ከልማትና ማቋቋም ዳይሬክቶሬት ፣ ከዕቅድ ፋይናንስና ሰው ሀብት አመራር ዳይሬክተር እና ከበሽታ መከላከልና የህክምና አገልግሎት ዳይሬክቶሬቶች አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

15. በተጨማሪም በማዕከል በሚገኙ የልማት ገቢዎች ከሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ቤት፣ ከዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ቤት ፣ ከድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት፣ ከአዲስ አበባ ከፍተኛ ጥበቃ ማረሚያ ቤት እና ከአዲስ አበባ ቀጠሮ ማረፊያ ቤት ኃላፊዎች እና ከታራሚዎች በአካል በመገኘትና ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም አስፈላጊ መረጃዎችን በመከለስ ለክዋኔ ኦዲቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ “በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብ፣ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ ክትትልና አፈጻጸም ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ” የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ ጭብጦች (Audit Issue)

17. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አከባቢ ሥር ሦስት የኦዲት ጭብጦች (Audit Issue) ተመርጠዋል፡፡ እነሱም፡-

ሀ. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ፤ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ ክትትልና አፈጻጸም ስርአት በመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያዎች የሚከናወን ስለመሆኑ ማጣራት፤

ለ. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ፤ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ ክትትልና አፈጻጸም ስርአት ላይ ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ሥራ የሚያከናውን ስለመሆኑ ማጣራት፤

ሐ. በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ፤ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ ክትትልና አፈጻጸም ላይ ተገቢው የመረጃ አያያዝ ስለመኖሩ ማጣራት የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/

18. ለዝርዝር ኦዲቱ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative Criteria/ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር (Proclamation No. 648/2009) አዋጅ እና ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ መመሪያ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት አቅጣጫዎች 20 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ በቅድሚያ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የስራ ኃላፊዎች ተልከው አስተያየት እንዲሰጡባቸው ተደርገዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶችም በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

<u>**የአሰራር ስርዓት መግለጫ**</u>

19. በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብ እና አሻሻጥ የአሰራር ስርዓት መግለጫ፡-



ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ ምርቶች አያያዝና የመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታን በተመለከተ፣

20. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ የግብርና ምርቶችን አሠባሠብ አያያዝና በመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታን አስመልክቶ ተገቢውን ጥናት በማካሄድ በቅድሚያ ሊያውቅ ይገባል፡፡
21. በኦዲቱ ወቅት በተካሄደ የመስክ ጉብኝት የመረጃ ክለሳና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ እንደተቻለው፣ በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል በ 2005 ዓ.ም በመጋቢት ወር ገበያ ለመቅረብ የደረሰ የሽንኩርት ማሳ መነቀል የነበረበት ከ 1 ወር በፊት ቢሆንም፣ በወቅቱ ባለመነቀሉ 250 ኩንታል የሚሆን ሽንኩርት በማሳው ላይ እያለ መበላሸቱን በመስክ ጉብኝቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡
22. በተመሳሳይ መልኩ ማዕከሉ በማሳ ላይ የደረሱ ምርቶች መቼ ተሰብስበው ለገበያ ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት ሊያስገኙ እንደሚችሉ በጥናት ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ባለመስጠቱ በጾም ወቅት ተፈላጊ የነበሩ ምርቶችን ለፋሲካ በዓል ጥቂት ቀናት ሲቀረው ከምርቱ ተረካቢዎች ጋር አስፈላጊውን ትዕዛዝና ቀብድ ሳይቀበል በቁጥር 1012 የጥቅል ጎመን ምርቶች ከማሳ ላይ እንዲሰበሰቡ በመደረጉ ምርቱ ገዢ በማጣቱ በብልሽት ምክንያት እንዲወገድ በመደረጉ ሊገኝ ይችል የነበረውን ብር 3542.00 /ሦስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ሁለት ብር/ ገቢ መታጣቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
23. በተጨማሪም በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል እርሻ ልማት ማሳ ላይ በ2005 ዓ.ም ከተመረተው ጥቅል ጎመን ውስጥ በቁጥር 1225 /አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አምስት/ ሳይሸጥ በመቅረቱ እና በመበላሸቱ ብር 4195 /አራት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና አምስት ብር ገቢ ስለመታጣቱ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሰ ቃለ ጉባኤ ለመረዳት ተችሏል፡፡

24. ስለሁኔታው የዝዋይ ተሐድሶና ልማት ዘርፍ አስተባባሪ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ፣ ሽንኩርቱ ከማሳው መነቀል የነበረበት ከአንድ ወር በፊት ቢሆንም፣ በገበያ እጦት የተነሳ ከማሳው ላይ ሳይነቀል የቀረ በመሆኑ ለብልሽት መዳረጉን አስረድተዋል፡፡

ፎቶ 1 በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል የደረሰው 250 ኩንታል ሽንኩርት በወቅቱ ሳይነቀል በመቅረቱ በማሳው ላይ እያለ የተበላሸ ሽንኩርት፡፡

25. በኦዲቱ ወቅት የተወገደውን ጥቅል ኅመን አስመልክቶ የዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ኃላፊ ተጠይቀው፤ በሰጡት መልስ፣ ለምርት ሽያጭ ሠራተኞች ከአቅም በላይ የሆነ ምርት በመቅረቡ የገበያውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያላስገባና ምርቱ ከመጠን በላይ በመሆኑና በአከባቢ ገበያ ሊሸጥ ባለመቻሉ እና ካለ ትዕዛዝም ከማሳ በመቆረጡ መሆኑን እና ኃላፊው በወቅቱ በዓል ለማሳለፍ ወደ ቤተሰብ መሄዳቸውን እና ሆኖም ድርጊቱን የፈጸመው ሠራተኛ ተጠያቂ በማድረግ ከቦታው እንዲነሳ እርምጃ መውሰዳቸውን ገልጸዋል፡፡

26. በተመሳሳይ በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል በተካሄደው የመስክ ጉብኝት፤ መረጃ ክለሳ እና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተበላሹ እና መሸጥ የማይችሉ የቲማቲም ምርቶች ከማሳ መለቀማቸው እና ምርት አቅራቢው ለሽያጭ በሚያመችና አዋጪ በሆነ መልክ ምርቶችን አደራጅቶ ባለማቅረቡ እና እንዲሁም የሽያጭ ሰራተኛው ምርቱ እየተሸጠ አለመሆኑን

ቢያሳውቅም፤ ያልተሸጠ ምርት እያለ ምርት አቅራቢው ምርት ስለሚያቀርብ ምርቱ እየተበላሸ ለብክነት በመጋለጡ በዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጥ እና አልሸጥ ካለም ተወግዶ ለአሳማዎች መኖ እንደሚውል ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. እንዲሁም የደረሱ ምርቶችን ማዕከሉ ለሸያጭ ማዋል ባለመቻሉ የቲማቲም ምርት በማሳው ላይ እየበሰበሰ መርገፉና ለብክነት መዳረጉን፤ የመሸጫው ሱቅ ውስጥ ሰፋፊ ቀዳዳዎች በመኖራቸው ምርቱ በአይጥ እና በተባይ እየተበላ ማስቸገሩ፤ የምርት መሸጫው ሱቅ ጣሪያው ዝናብ ማስገባቱ እና ምርት ማበላሸቱን፤ የምርት መሸጫው ሱቅ ከበሩ ስር ክፍት መሆኑ እና ለስርቆት ሊዳርግ እንደሚችል፤ መጋዘኑ የአይጥ ጎሬ መሆኑ እና ምርቱን እያበላሹ መሆናቸውና ከማሳ ላይ የምርቱን ግዜ ጠብቆ አለማስነቀል እንደ አንድ መሠረታዊ ችግር መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት በተደረገው የመስክ ጉብኝት ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፎቶ 2 የሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል የምርት መሸጫው ሱቅ ጣሪያው ዝናብ ማስገባቱ፤ የመሸጫው ሱቅ ከበሩ ስር ክፍት መሆኑ፤ ለስርቆት ሊዳርግ እንደሚችል፤ ሰፋፊ ቀዳዳዎች በመኖራቸው አይጦችን እንደሚያስገቡና አጠቃላይ የመሸጫ ሱቁን ሁኔታ የሚያሳይ ፎቶ፡

28. ከዚህ በተጨማሪም በሸዋሮቢት ማረሚያ ቤት የግብርና ምርቶች ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ከሶስት አመት በፊት ጊዜው ያለፈበት አደገኛ ኬሚካል (Bayleton 25 WP) ከተለያዩ ምርቶች (ቲማቲም፤ ማንጎ፤ በቆሎ.....ከመሳሰሉት) ጋር መቀመጡና በምርቱ ላይ እና በመጋዘኑ ሰራተኞች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፤ ኬሚካሉ እንዲወገድላቸው የመጋዘኑ ሠራተኞች ለማረሚያ ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቃል

በተደጋጋሚ እንደጠየቁና መልስ ማጣታቸውን፤ በቃለ መጠይቅ ወቅት የገለጹ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅትም ችግሩ አለመፈታቱን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ፎቶ 3 የሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ምርት መጋዘን ጊዜው ያለፈበት አደገኛ ኬሚካል ከተለያዩ ምርቶች ጋር መቀመጡና አጠቃላይ የመጋዘኑን ሁኔታ የሚያሳይ ፎቶ፡፡

29. ስለሁኔታው ለሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ በማዕከሉ የምርት ማሳያ እና መሸጫ ቦታ ጥበት በመኖሩ የመጣ ችግር መሆኑና ጊዜው ያለፈበት አደገኛ ኬሚካልን በተመለከተ ለማስወገድ በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

30. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊ፤ ለብልሽት የተጋለጡ ምርቶች እና የመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታዎች መግለጫ ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ የተነሱት ሃሳቦች በተለይ በጓሮ አትክልት ሽንኩርት፤ ጥቅል ጎመንና ቲማቲም ምርቶች ላይ የምርት አመራረት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ በሁለቱም በዝዋይ እና በሸዋሮቢት ተሃድሶ ልማት ማረሚያ ማዕከል በኦዲቱ የተገለጹት ችግሮች እንደነበሩ የሚታመኑ መሆናቸውንና እነዚህም ችግሮች ቀደም ሲል የምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ መመሪያ ከመዘጋጀቱ በፊት የነበሩና መመሪያውም በ 2004 ዓ.ም ከተዘጋጀ በኋላ ለማረሚያ ቤቶች ማዕከላት እንዲደርስ ቢደረግም መመሪያውን ተግባራዊ ካለማድረግ የተፈጠሩ ችግሮች መሆናቸውና ለነዚህም ችግሮች በተለይ በዝዋይ ተሃድሶ ልማት ማረሚያ ማዕከል በምርት አቀራረብ ላይ የተስተዋለ የጥቅል ጎመንና የቀይ ሽንኩርት ምርት

አቀራረብ ሂደት በመመሪያው መሠረት ያልተከናወነ በመሆኑ ሥህተቱን በፈጸሙ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ላይ ጉዳዩን በማጣራት አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰዱን ገልጸዋል፡፡

31. እንዲሁም በሸዋሮቢት ማረሚያ ማዕከል በወቅቱ የተፈጠረ በዋናነት የምርት አሻሻጥ ገበያና ተመን አወሳሰን የባለቤትነትና የተጠያቂነት ችግር ምክንያት በማሳ ላይ የደረሰ የቲማቲም ምርት ለብልሽት መዳረጉን እና ይህንንም ችግር በማጣራት ጉዳዩ በሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች በየጊዜው በሚደረግ ክትትልና ድጋፍ በቀጣይ ችግሩ እንዲወገድ እየተሠራ መሆኑን እና በአጠቃላይ በዕቅድና በአመራረት ሂደት ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን በተለያዩ ሥልጠናዎችና ከሌሎች ተባባሪ የግብርና ምርምር ማዕከላት ጋር በጋራ በመስራት እና በመደጋገፍ ምርትና ምርታማነትን የማሻሻል ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ላይ ገልጸዋል፡፡

32. በተጨማሪም በምርት አሻሻጥ ሂደት በምርት ማቆያ፣ ማሳያና መሸጫ፣ መጋዘን እና ሱቅ በርክክብና በአሻሻጥ የተከሰቱ ችግሮች በአጠቃላይ ደረጃውን የጠበቀ የምርት ማቆያና መሸጫ ክፍሎች የሌሉ መሆናቸው እንደሚታወቁ እና በነዚህም ምክንያት በምርት አሻሻጥ ላይ ብክነትና ብልሽት እንደሚከሰት እና ኦዲቱ ያቀረባቸውን ችግሮች በመቀበል በቀጣይ ለመቅረፍ በጀት ተይዞ የግንባታ ሥራዎችን መስራት አስፈላጊነቱ እንደሚታመን፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አሰተያየት ሰጥተዋል፡፡

33. በአጠቃላይ ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ የግብርና ምርቶች ከአሠባሰብ አያያዝና የመጋዘን አቀማመጥን አስመልክቶ በዝዋይ እና በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከላት ያለው አሠራር በተገቢው ጥናት ላይ ያልተመሠረተ፣ በስራ ክፍሎች ያለው ትስስር ያልተጠናከረ የመጋዘኖቹና የሽያጭ ቦታዎች አስፈላጊውን ደረጃ ባለሟሟላታቸው የሚመረቱ የግብርና ምርቶች ለብክነት እና ለብልሽት እንዲዳረጉ በማድረግ ማዕከላቱ ሊሰበስቡ ይችል የነበረውን ገቢ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጓል፡፡

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፍቃድ የሰጠው ወይም ያሳተመው መሆኑን በተመለከተ፤

34. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ማዕከላት ከውስጥ ገቢ የሚሰበስቡትን ገንዘብ ገቢ የሚያደርጉበት ደረሰኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም ፍቃድ በሰጠው ደረሰኝ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት በመስክ ስራ ከታዩት የዝዋይ፣ የሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል እና የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል በተካሄዱ የመረጃ ክለሳና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ፣ ከማዕከላቱ የውስጥ ገቢ የሚሰበሰበው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ደረሰኝ ቢሆንም፣ ማዕከላቱ ለሚያካሂዱት የግብርናና ሌሎች ምርቶች ሽያጭ ለገዢዎች ደረሰኝ እንደማይሰጡ ታውቋል፡፡

36. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ገንዘብ መቀበያ ደረሰኙ ላይ ታክስ የሚል ቀደም ብሎ የተጻፈ ጽሁፍ ስለሌለ፤ የከፈለበት ምክንያት የሚለው ቦታ አጠገብ ላይ በእጅ ጽሁፍ "ታክስ" የሚል በማስገባት የምርቱ ዋጋ ላይ 5% በመጨመር እንደሚያሰሉና ለዚህም ታክስ ምንነት ምክንያት እንዲያስረዱ ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

37. ስለሁኔታው በናሙና በተመረጡ የዝዋይ፣ የሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል እንዲሁም የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል ዕቅድ ፋይናንስና ሰው ሀብት አስተባባሪ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ ለተቀበሉበት ገንዘብ ደረሰኝ የሚሰጡት ለጅምላ ገዢ ብቻ መሆኑንና ለችርቻሮ ተገልጋይ ግን ለሁሉም ደረሰኝ መቁረጡ ደረሰኝ ከማባከን አንጻር እንደማይሰጡ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን የገንዘብ መቀበያ ደረሰኙን እንደ ገቢ ማጠቃለያ በመቁረጥ እንደሚጠቀሙበት አስረድተዋል፡፡

38. በተጨማሪም የ 5% ታክስ መነሻ ምክንያት ለተጠየቁት፤ ከድሮ ጀምሮ የሚሰራበትና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ደረሰኝ ላይ ታክስ ተብሎ የተጻፈ ባለመኖሩ በእጅ ጽሁፍ በእስኪብርቶ ደረሰኙ ላይ እየጻፉ እንደሚሰበስቡና የልማቱ ገቢም ሆነ የተሰበሰበው ታክስ በዋናው መስሪያ ቤት ተለይቶ ባለመያዙ፣ የተሰበሰበውን ታክስ ከልማቱ ገቢ ጋር በመቀላቀል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

39. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊ፣ በነባራዊ ሁኔታው መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ የዕለት ገንዘብ የሚሰበሰበው በገቢ ደረሰኝ በመሂ/1 ሲሆን፣ በጥቅል ለሚገዙ ነጋዴዎች የዚህኑ ደረሰኝ የመጀመሪያውን ገጽ እንደሚሰጡና በተንጠባጠበ መልኩ ለሚሸጠው ግዥዎች ግን ለእያንዳንዱ መሂ/1 ለመቁረጥ በመሂ/1 ላይ ያለው እጥረት በሰፊው ስለሚታይ፣ ሽጬም ቀደም ሲል በተረከበው የምርት መረከቢያ ቅጽ በመታገዝ አጠቃሎ የመመዝገብ አሰራር እየተጠቀሙ ቁጥጥሩን በማድረግ የሚሰራ መሆኑን እና ከዚህ በተለየ የሚሰጣቸው እርምት ካለ እንደግብዓት በቀጣይ እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል፡፡

40. በተጨማሪም በማዕከሎቻቸው በምርት ሽያጭ ወቅት በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ ታክስ የሚል ሳይኖር የምርቱ ዋጋ ላይ 5% ታክስ የሚል ጽሮ በእጅ ጽሁፍ ጽፎ በማስላት ሽያጩ የሚካሄድበት ምክንያት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ቀደም ሲል ካሉ ረዥም ጊዜያቶች ጀምሮ የሚሰራባቸው በዚህ መልኩ በመሆኑና፣ ይህንኑ አሁንም ተከትለው መሄዳቸውን እና እንዲሁም መሂ/1 የመንግሥት የገቢ መሰብሰቢያ በመሆኑ በተለየ መልኩ ማሳተም የማይፈቀድ ስለሆነ በአሁን ወቅት መመሪያው በእጃቸው ባይኖርም ታክሱ እንዲሰበሰብ የታዘዘውን ተዕዛዝ ላለመጣስ በእጅ ጽሁፍ ታክስ ብሎ በመጻፍ እየሰበሰቡ መሆናቸውንና ለዚህም የሚሰጣቸውን እርምት በአስቸኳይ ወደ ተግባር የሚተረጉሙ መሆናቸውን እንዲታወቅላቸው የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አሰተያየት ሰጥተዋል፡፡

41. በዝዋይ፣ በሸዋሮቢት እና በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤቶች በሚያካሂዷቸው የግብርናና ሌሎች ምርቶች ሽያጭ ለችርቻሮ ገዢዎች ህጋዊ ደረሰኝ አለመስጠታቸው እንዲሁም በሚጠቀሙባቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ላይ በህግ ከተፈቀደው ውጭ የ 5% ታክስ መሰብሰባቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የውስጥ ገቢ አሰባሰብን መርህን ያልተከተሉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>በማዕከላት ከምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ መደረጉን በተመለከተ፣</u>

42. በማዕከላት በምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

43. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የመስክ ስራ፣ የመረጃ ክለሳና ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ በዝዋይ እና በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል በምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ አይደረግም፡፡ በዝዋይ

ከ1/07/2005 እስከ 8/07/2005 ከሽያጭ የተሰበሰበ ገቢ በ 9/07/2005 ማለትም ከሳምንት በኋላ ብር 28,074.00 (ሃያ ስምንት ሺ መቶ ሰባ አራት) ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. ስለ ጉዳዩ የዝዋይ እና ሽዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከላት የዕቅድ ፋይናንስና ሰው ሀብት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ በምርት ሽያጭ የሚሰበሰበው ገንዘብ በዕለቱ ገቢ እንደሚደረግ እና ነገር ግን አንዳንዴ ምርት በብዛት ሲመጣ የሽያጭ ሰራተኞቹ ስራ ስለሚበዛባቸው በየቀኑ ገቢ የማይደረግበት ጊዜ መኖሩን እና ሻጩ በየቀኑ የሸጠውን ከቀኑ በ 10፡00 ሰዓት ባንክ እንደሚያስገባ እና የገቢ አሰባሰብ እና ገቢ አደራረግ ስርዓቱ በመመሪያው መሰረት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

45. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ስለ ሁኔታው ተጠይቀው፤ በምርት ሽያጭ የተሰበሰበውን ገንዘብ በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ ያለመደረጉ ምክንያት ሁኔታ አልፎ አልፎ የሚታይ መሆኑን እና ይህም የሚሆንበት ምክንያት ምርቶቻቸውን በብዛት ከማሳ ላይ በሚነሱበት ወቅት የጊዜ እጥረት እየገጠማቸው ሽያጩም በዚህ መልኩ ከባንክ መዝጊያ ሰዓት ውጪ በመጠናቀቁ መሆኑን ይህንንም አሠራር ቀይረው ሰዓቱ ተጠብቆ የዕለት ገቢ ሂሳቡ በዕለቱ ወደ ባንክ እንዲገባ እንዲያደርጉ ጥብቅ ትዕዛዝ/መመሪያ/ በማስተላለፍ ክትትል የሚያደርጉና ከዚህ በኋላ የማይደገም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

46. በዝዋይና በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከላት ከምርት ሽያጭ የሚሰበሰበው ገቢ በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ አለመደረጉ የመንግሥት መመሪያን ያልተከተለና የማዕከላቱ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ስርዓቱ መጣሱ ለብልሹ አሠራር ክፍተት እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡

<u>በማዕከላት ከምርት አሠባሰብ እስከ ሽያጭ ሂደትን የመከታተያ ስርዓትን በተመለከተ</u>፤

47. የምርት ማቅረቢያ ማዘዣ ምርት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት ፤ ደረጃ ፤ መጠን ፤ የአቅርቦት እለትና ሰዓት ፤ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ ማዕከላት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

48. በናሙና በተመረጡ ማዕከላት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት ፤ ደረጃ ፤ መጠን ፤ የአቅርቦት እለትና ሰዓት ፤ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ

በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ የሚጠቀሙበት አሰራር የለም፡፡

49. በዝዋይ እና በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ርክክቡ የሚፈጸምበትን ቀንና ቦታ ከማመቻቸት እና ለአስረካቢ ኮሚቴ ከማሳወቅ አንጻር ወቅታዊ አለመሆኑ እና የቲማቲም እና የሽንኩርት ምርት በርክክብ ወቅት ያለው የሚዛን መጠንና፣ መሸጫ ሱቅ በሚገባበት ጊዜ ያለው ሚዛን መለያየቱና ቲማቲሙ እና ሽንኩርቱ በፍሰት እና ሲያድር ሊያወጣ የሚችለውን የሚዛን ጉድለት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ፣ እና ሻጮች ሚዛኑ ሲጎልባቸው ከላይ የተገለጹት ምክንያቶች ግንዛቤ ውስጥ ባለመግባቱ ሻጮች ከኪሳቸው እንደሚከፍሉ የምርት አስረካቢ እና የምርት ሻጮች በኦዲቱ ወቅት ገልጸዋል፡፡

50. ይህን በተመለከተ የማዕከላቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፣ በርክክብ ወቅት ያለው የሚዛን መጠንና፣ መሸጫ ሱቅ በሚገባበት ጊዜ ያለው ሚዛን መጠን እንደሚለያይ ቢያውቁትም ከአሰራር እና ከመመሪያ አንጻር መጨመርም ሆነ መቀነስ ስለማይቻል ችግሩን ለመፍታት እንዳልቻሉ አስረድተዋል፡፡

51. ይህን ይበሉ እንጂ ምርት ለተጠቃሚ በቀጥታ ሲሸጥ የሚያስከትለውን የሠራተኛ ወጪ፣ መጓጓዣና ብክነት ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ መሆኑን በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የግብርና ምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ መመሪያ በአንቀጽ 18 ላይ የተቀመጠ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

52. በተጨማሪም በምርት አሻሻጥ ሂደት የምርት ሻጭ ፈሰስ /መጠባበቂያ/ በእነዚህ ዙሪያ በኦዲቱ የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል የሚቀርፍና የሚያሻሽል አሠራር በመዘርጋት በቀጣይ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

53. እንዲሁም በኦዲቱ የምርት ማቅረቢያ ማዘዣ ምርት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት ፣ ደረጃ ፣ መጠን ፣ የአቅርቦት እለትና ሰዓት ፣ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ ባለመጠቀማቸው የሸዋሮቢት እና የዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከላት ለሻጮች ምርት የሚቀርብላቸው ጠዋት ከአራት ሰአት (4፡00) በኋላ መሆኑና በዚህም ምክንያት የገበያ ሰአት ስለሚያልፍ ምርቱ ሳይሸጥ ለብክነት መዳረጉ እና በወቅቱ እንዳይሸጥ አስተዋጽኦ ማድረጉ ታውቋል፡፡

54. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊ የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ ተረካቢ፣ አሰረካቢ እና አረካካቢ መረጃን በመለዋወጥ በተወሰነ ሰአትና ቦታ በመገናኘት የሚከናወን ሲሆን፣ የመረጃ ዕጥረት አለመኖሩን እና ነገር ግን የኦዲት ቡድኑ የምልከታ ሥራውን ሲያከናውን ተከስቶ ሊሆን ስለሚችል በቀጣይ ለሥራው የሚመደቡ ኮሚቴ አባላት ትኩረት ማነስ እና በመሳሰሉት ምክንያት ችግሮች እንዳይከሰቱ የኦዲት ቡድኑን አስተያየት በግብአትነት በመውሰድ የክትትልና ድጋፍ ስራ በቀጣይ የሚሠራ ይሆናል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

የማረሚያ ቤቱን ምርት ለመሸጥ የማስተዋወቅ ስራን በተመለከተ፣

55. የማዕከላት አምራቾች የሚሸጡትን ምርቶች አይነትና የሽያጭ ፕሮግራም ለደንበኞች በግልጽ በሚታይ ቦታ ማስታወቂያ መለጠፍና እንደአስፈላጊነቱ በሚዲያ ሊያስነግሩ ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጂ በናሙና በተመረጡ ማዕከላት ለደንበኞች ምርቱን ለመሸጥ የማስተዋወቅ ስራ አለመሰራታቸው እና የምርት አሻሻጥ፣ ተግባራትና ዘዴዎቹ ግልጽ አለመሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ከ 1250 ኩንታል በላይ ሽንኩርት አምርተው ገበያ ያጡበት ወቅት መኖሩ እና በሁለቱም መዕከላት ማለትም በሸዋሮቢት እና በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ከገበያ ዕጦት የተነሳ ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ እና በመጠነኛ የተጋለጡ ምርቶችን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጡ በማድረግ እና አልሸጥም ካለም እንዲወገድ ምክንያት ሆኗል፡፡

ፎቶ 4 በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ከገበያ ዕጦት የተነሳ ለብልሽት ተጋልጦ እንዲወገድ የተደረገ ሽንኩርት፡፡

57. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት፣ ለየማዕከላቱ የምርት አስረካቢ፣ የምርት ዋጋ ተማኝ እና የምርት አስወጋጅ ኮሚቴ እንዲሁም የማእከሉ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ የምርት አሻሻጥ፣ ተግባራትና ዘዴዎቹ ግልጽ አለመሆናቸው እና በማረሚያ ቤቱ ውስጥ የሚለሙ ምርቶች በሙሉ ለገዥው ግልጽ በሆነ መንገድ አለማስተዋወቃቸውን፣ ምርቱን የሚያሳዩበት የቦታ ጥበት መኖሩ፣ ምርትን ለማሳየት የሚያስችል ሱቅ አለመኖሩ፣ ማስታወቂያ በይፋ አለመነገሩ፣ የማስተዋወቂያ ዘዴዎቻቸው ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ቲማቲም በመጋቢት 13/2005 ዓ.ም በገበያ ዋጋ ብር 8.00 (ስምንት) እየተሸጠ በማእከሉ ግን በ 3.00 (ሶስት) ብር መሸጥ አለመቻላቸው (ሸዋሮቢት)፣ እንዲሁም ሽንኩርት በ 1.60 ሳንቲም (በአንድ ብር ከስልሳ ሳንቲም) መሸጥ እንዳልቻሉ (ዝዋይ) እና የማስተዋወቅ ስራን አለመስራታችን በተመለከተ እንደ ድክመት ሊቆጠር ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል ፡፡ ሆኖም ግን በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት ላይ በከተማው የማስታወቂያ ቦርድ ላይ የማእከሉን ምርትና ዋጋ መለጠፍ መጀመራቸውን እና የማስተዋወቂያ ስራዎች መጀመራቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡

58. በተጨማሪም በሸዋሮቢት እና በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል የምርት አሻሻጥ ዘዴዎችን በተመለከተ ለአባላቱና ለአባላቱ ቅርበት ላላቸው ሰዎች የሚሸጥ ሲሆን፣ ሌላው በዝዋይ ማእከል ውስጥ በደላላ አማካኝነት ለነጋዴው በጅምላ እና በከተማው ውስጥ አንዳንዴ በመኪና በማዘዋወር እንደሚሸጡና፣ መሸጫ ሱቃቸውን

በተመለከተ ከተማው ውስጥ ሁለት (2) ሱቅ እንዳላቸው እና አንደኛው ግን ባሁን ወቅት ብዙ ምርት ስለሌላቸው በሚል የተከራየ መሆኑ እና በአንደኛው ሱቅ ደግሞ ምርት በብዛት ሲኖር ምርቱን እንደሚሸጡበት እና የምርት ማቆያ መጋዘን እንደሌላቸው የማዕከላቱ ኮሚቴዎች እና ኃላፊዎች አስረድተዋል፡፡

ፎቶ 5 በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል የምርት ማቆያ መጋዘን ባለመኖሩ መሬት ላይ ሲረካከቡ እና ለሽያጭ ሲውል የሚያሳይ ፎቶ፡፡

59. ይሁን እንጂ የማረሚያ ቤቱን ምርት በተገቢው መልኩ ለመሸጥ የማስተዋወቂያ ስራ አለመሰራቱ እና በኦዲቱ ጉብኝት ወቅት በማዕከሉ የመሸጫ ቦታ ጥበት ምክንያት መሬት ላይ ወተትን ጨምሮ ሌሎች ምርቶችን ሲሸጡ እና የምርት ማቆያ መጋዘን ሳይዘጋጅ በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ካሉት ሁለት ሱቆች ውስጥ አንደኛው፤ “ምርት በብዛት ሰለሌለ አከራይተነዋል” ተብሎ የተሰጠውን መልስ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

60. በተጨማሪም ለአባላቱና ለአባላቱ ቅርበት ላላቸው ሰዎች ምርትን መሸጥ በተለይም የኢንዱስትሪ ምርቶችን፤ በምርት ሽያጭ ሂደት ደንበኞች ፍትሀዊ አገልግሎት የሚያገኙበት መንገድን ከማመቻቸት አንጻር በአስተዳደሩ ከተቀመጠው ከምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ መመሪያ መርሆ ጋር የተጋጨ ነው፡፡

61. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊ፣ የምርት አሻሻጥን ማስታወቂያ ማስነገር እና ከማረሚያ ቤቱ ውጪ ላለው ህብረተሰብ በቀላሉ የግዢ ተጠቃሚ የሚሆኑበት እና ተቋማቸውንን ከዚህ ተጠቃሚ ማድረግ አግባብ እንደሆነና በተለያየ ምክንያት አለመከናወኑን እና ይሁን እንጂ በቀጣይ እነዚህን ችግሮች በተቻለ መጠን ለመቅረፍ በአስተዳደሩ ህዝብ ግንኙነት በኩል መስራት እንዳለባቸው ተረድተናል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

62. ስለሆነም የሚሸጡ ምርቶች ማስተዋወቂያ ዘዴዎች በውስጥ ማስታወቂያ፣ በብዙሃን መገናኛ /ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ጋዜጣ/፣ በመ/ቤቱ ድረ-ገጽና በአውደ ራዕይ ሊያስተዋውቅ ይችላል ተብሎ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የግብርና ምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ መመሪያ አንቀጽ ሠላሣ (30) ላይ ቢቀመጥም በማዕከላቱ የሚመረቱ ምርቶችን በተገቢው መንገድ በማስተዋወቂያ ስራ ባለመሰራቱ በገበያ ዕጦት ምክንያት የተመረቱ ምርቶች በዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጡ እና ገዢ ሲጠፋም በብልሽት የሚወገዱበት ሁኔታ እንዲኖር እና የማዕከላቱ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጓል፡፡

<u>የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ መመሪያ ማዘጋጀቱን እና ለሚመለከታቸው ማዕከላት ማሰራጨቱን በተመለከተ፣</u>

63. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ መመሪያ ሊያዘጋጅና ለሚመለከታቸው ማዕከላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በመመሪያው ዓላማ መሠረት ማዕከላቶች ትርፋማና በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይገባቸዋል፡፡

64. ይሁን እንጂ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለግብርና ምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ ተፈጻሚነቱ በአስተዳደሩ ስር ለሚገኙ ለዝዋይ፣ ለድሬዳዋ እና ለሸዋሮቢት ማረሚያ ቤቶች እንዲውል መመሪያ አውጥቶ ለማዕከላቱ ቢያሰራጭም ተግባራዊ ለመሆኑ ክትትልና ድጋፍ አልተደረገም፡፡

65. እንዲሁም በናሙና የተመረጡ የማዕከል ኃላፊዎችም ሆኑ ከምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብ እስከ አሻሻጥ ድረስ የተሰየሙት ኮሚቴዎች የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የተሃድሶ ልማቱ አገልግሎት አላማ ማረም እና ማነጽ ነው እንጂ "ትርፋማ እንዲሆን አይደለም" የሚል አመለካከት እንዳላቸው በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

66. ይሁን እንጂ "የአስተዳደሩ ተሃድሶና ልማት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የሚመረቱ የግብርና ምርቶች ትርፋማና በገበያ ተወዳዳሪነት ያላቸው እንዲሆኑ ማስቻል" ነው

ተብሎ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ እና አሻሻጥ መመሪያ አንቀጽ አራት (4) ላይ በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ፤ በናሙና የተመረጡ የማዕከል ኃላፊዎችም ሆኑ ከምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ እስከ አሻሻጥ ድረስ የተሰየሙት ኮሚቴዎች የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር አላማ ማረም እና ማነጽ ነው እንጂ ትርፋማ እንዲሆን አይደለም የሚለውን አመለካከታቸውን አልተቀበልነውም፡፡

67. በሌላም በኩል የኢንዱስትሪ ምርቶች በማዕከሉ ቢመረቱም በማዕከላቱ መሸጫ ሱቅ እንደማይቀርቡ እና እዛው ማምረቻ ውስጥ (ስልጠና ክፍል ውስጥ) ለአባላቱ እንደሚሸጡና፤ የአሻሻጡም ሁኔታ በተመለከተ የኢንዱስትሪ ምርት አሻሻጥ መመሪያ አለመኖሩን በኦዲቱ ታውቋል፡፡

68. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ቀደም ሲል የነበሩ የምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ እና አሻሻጥ ችግሮች በግምገማ ከተለዩ በኋላ ለዚህም መፍትሄ ለመፈለግ ከተቋሙ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ታስቦ የግብርና ምርት አሰባሰብ ፤ አቀራረብ እና አሻሻጥ መመሪያ ሲዘጋጅ ማዕከላትን የመረጃ ምንጭ በማድረግ በጉዳዩ የማሳተፍ ሥራ የተሠራ ሲሆን ረቂቅ መመሪያው ከተዘጋጀ በኋላ ወደ ሁሉም ማረሚያ ማዕከላት ተልኮ በማስተቸት የማስተካከያ ሃሳብ ዳግም መሰብሰቡን እና ከጸደቀ በኋላም ጉዳዩ በዋናነት የሚመለከታቸውን ሃላፊዎችና ባለሙያዎች በዋናው መስሪያ ቤትና በማዕከል ደረጃ ለሁሉም በጋራ ሥልጠና ከተሰጠ በኋላ በየደረጀው የሠለጠኑት ላልሰለጠኑት በሂደት ግንዛቤ በመስጠት መመሪያውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለሁሉም ማረሚያ ማዕከላት መመሪያው ሥራ ላይ እንዲውል በአስተዳደሩ በበላይ ኃላፊ ጸድቆ መላኩን እና ሆኖም ግን የመመሪያውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የክትትልና ድጋፍ የማድረግ እጥረት መኖሩን ተረድተን የአጭር ጊዜ ዕቅድ ተዘጋጅቶ እየተሰራ ይገኛል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አሰተያየት ሰጥተዋል፡፡

69. እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ምርቶች አሻሻጥ መመሪያ አለመዘጋጀቱን በተመለከተ መመሪያውን ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ የታመነበት ሲሆን መመሪያውን ለማዘጋጀት ግብአት የማሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል በማለት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ላይ አሰተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

70. በተጨማሪም አስተዳደሩ በተሃድሶና ልማት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የሚመረቱ የግብርና ምርቶች ትርፋማና በገበያ ተወዳዳሪነት ያላቸው እንዲሆኑ ማስቻል የሚል መርህ የያዘ ሲሆን ትርፉ ግን ሁለት መልክ ያለው መሆኑን እና አንደኛው አዲስ

የግብርና ልማት ቴክኖሎጂ ሽግግርና ስርጸት የማፋጠን ሥራ በህግ ታራሚው ዘንድ በማስፋት ታራሚው የሚገበየው የግብርና ልማት ሥራ ዕውቀትና ክህሎት ሲሆን ይህንንም ለማስተማር በገበያ ተወዳዳሪ መሆን ግድ ስለሚል ሁለተኛው የሚመረቱ ምርቶች ትርፋማ እና አዋጪ ሆኖ መገኘት በመሆኑ ስለዚህ ውጤታማ ማረም፣ ማነጽ እና በግብርና ሂደት በሚመረቱ ምርቶች ትርፋማ፣ አዋጪና በገበያም ተወዳዳሪ መሆን የሚነጣጠሉ አይደሉም በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አሰተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

71. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ የምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብ እና አሻሻጥ መመሪያ ቢያዘጋጅም ለሚመለከታቸው ማዕከላት ባለማሰራጨቱ የምርት አሠባሠብ ሂደት ተግባራትን፣ የምርት አሻሻጥ ተግባራትን፣ የግብርና ምርት የአሻሻጥ ዘዴዎችን፣ አሻሻጥ ለማከናወን የሚደረጉ ተግባራትን፣ የኮሚቴዎች የስብሰባ ስርዓትን፣ የተከለከሉ አሠራሮችን፣ የተከለከሉ አሠራሮችን መፈጸም የሚያስከትሉት ቅጣት ዓይነቶች፣ የሽያጭ ወቅት ግዴታዎች፣ በምርት አሳባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾችን፣ የሚሸጡ ምርቶች ማስተዋወቂያ ዘዴዎችን፣ እና ትርፋማና በገበያም ተወዳዳሪ መሆናቸውን ማዕከላት እንዳያውቁት አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ምርት አሻሻጥ መመሪያ ባለመዘጋጀቱ የኢንዱስትሪ ወጤቶች አሻሻጥ በማዕከላቶች ግልጽ የሆነ አሰራር እንዳይኖር አድርጓል፡፡

<u>በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የውስጥ ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፣</u>

72. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ በኦዲትና ኢንስፔክሽን ጽ/ቤት ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡

73. በኦዲት ወቅት በናሙና በተመረጡ ማዕከላት የውስጥ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ ከስራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ በኦዲትና ኢንስፔክሽን ጽ/ቤት ኦዲት ተደርጎ እንደማያውቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

74. በተጨማሪም ለአብነት ያህል የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል የተሐድሶና ልማት ዘርፍ አስተባባሪ ፋይናንስ ከአባላቱ የምርት ሽያጭ ዱቤ የሰበሰውን በየወሩ በትክክል እየቆረጠ ፈሰስ እያደረገ ነው ወይ የሚለውን የሚያረጋግጥ የውስጥ ኦዲት አለመኖሩን እንደ ሥጋት ማየታቸውን ገልጸዋል፡፡

75. ስለጉዳዩ በናሙና በተመረጡ የዝዋይ፣ የሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል እንዲሁም የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል ዕቅድ ፋይናንስና ሰው ሀብት አስተባባሪ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የውስጥ ኦዲት በመዋቅሩ መሠረት የተመደበ ሰው ያለ ሲሆን በዝዋይ እና በሸዋሮቢት የገቢ አሰባሰብን በተመለከተ ኦዲት ተደርጎ እንደማያውቅ እና ለዚህም ምክንያት አንዱ በገቢ አሰባሰብ በውስጥ ኦዲት ላይ ስልጠና አለመሰጠቱ እና በውስጥ ኦዲት በዕቅድ አለመያዙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል በተመለከተ ደግሞ ለውስጥ ኦዲቱ የተመደበ ቢሆንም፣ ከሥራ ከለቀቀ አንድ አመት በመሆኑ የክዋኔ ኦዲቱ እየተከናወነ እስካለበት ወቅት ድረስ በምትኩ የማረሚያ ቤት አስተዳደር ቅጥር እንዳልፈጸመላቸው አስረድተዋል፡፡

76. በኦዲቱ ወቅት በተደረገው በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል የንብረት ክፍል ቢሮ ጉብኝት ወቅት፣ በሞዴል 19 (የገቢ መዝገብ) እና በሞዴል 22 (የወጪ መዝገብ) መዝገብ ላይ አንድ ሰው በንብረት ገቢና ወጪ ላይ ተመድቦ ሲሠራ ተገኝቷል፡፡ በእኛ አስተያየት የውስጥ ኦዲት በማዕከሉ ቢኖር ኖሮ ይህ ዓይነቱን አሰራር እንዳይሰሩና የስራ ክፍፍል ስርአቱን እያዛባ መሆኑን በማስገንዘብ መፍትሄ እንዲሰጥ ያደርግ እንደነበር እናምናለን፡፡

77. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል ንብረት ክፍል ውስጥ በንብረት ገቢ ሞዴል 19 እና በንብረት ወጪ ሞዴል 22 ሥራ ላይ አንድ አባል ተመድቦ እንዲሰራ የተደረገበት ምክንያት በቦታው ላይ ይሰሩ የነበሩት አባላቶች በተለያዩ ምክንያቶች መ/ቤቱን ለቀው የሄዱ በመሆኑና በተቋሙም የሠራተኛ እጥረት ያጋጠመ ስለሆነ እንዲሁም ቦታው ክፍት ቢሆን በሕግ ታራሚዎች ምግብና የተለያዩ ቁሳቁሶች ወጪ ላይ ችግር የሚያስከትልባቸው በመሆኑ ይህንን ለመቅረፍ ሲሉ የተደረገና ለወደፊት ግን በቦታው ላይ ሠራተኛ እንዲመደብ አስፈላጊውን ሁሉ የሚፈጽሙ መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

78. በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አሰተዳደር ማዕከላቶች በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የውስጥ ኦዲት ባለመደረጉ በውስጥ ኦዲት አሠባሰብ አሠራርና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመገምገምና ሥጋትን/ ተጋላጭነትን በመፈተሽ ለማዕከላቱ ተጨማሪ እሴት/ ፋይዳ በመሥራትና፣ ለሥራ አመራሩ የምክር አገልግሎት በመስጠት ለማረሚያ ቤቱ ዓላማ መሳካት ተጨማሪ አስተዋጽኦ እንዳያገኝ አድርጎታል፡፡

በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጻ ቅጾች መጠቀምን በተመለከተ፤

79. በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾች፡- የዋጋ ተመን የሚወጣላቸው ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 001፤ የዋጋ ተመን ጥናት መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽና ቃለ ጉባኤ ቅጽ 002፤ ለሽያጭ የሚቀርቡ ምርቶች መጠየቂያ ቅጽ 003፤ የተተመኑ ምርቶች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረጊያ ቅጽ 004፤ የዋጋ ማሻሻያ ተመን የተጠየቀባቸው የምርት ዓይነቶች ማሳወቂያ ቅጽ 005፤ በዋጋ ማሻሻያ ተመን ምክንያት ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ የሆኑ ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 006፤ የተበላሹ ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 007 እና የተበላሹ ምርቶች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ማሳወቂያ ቃለ ጉባኤ ቅጽ 008 የማረሚያ ቤት አምራቾች ቅጹን ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

80. ይሁን እንጂ በናሙና በተመረጡ በዝዋይ እና በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከላት በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾችን እንደማይጠቀሙ ለማጋገጥ ተችሏል፡፡

81. ስለጉዳዩ በናሙና በተመረጡ የዝዋይ እና የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከላት በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጻ ቅጾችን እንደማያውቋቸው የምርት አስረካቢ፤ የምርት ተማኝ፤ እና የምርት አስወጋጅ ኮሚቴዎች አስረድተዋል፡፡

82. እንዲሁም የዋጋ ተመን ጥናት መረጃ ማሰባሰቢያ እና በርክክብ ወቅት የምርት መጠንን የሚገልጽ መረጃዎች ሲቀርቡ፤ ለቁጥጥርና ተአማኒነት ባላቸው ሳይሆን፤ በነጭ ወረቀት ሲጠቀሙ በኦዲቱ በተደረገው የመስክ ጉብኝት ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾች (001፤ 002፤ 003፤ 004፤ 005፤ 006፤ 007 እና 008) በማተሚያ ቤት የታተሙ ሳይሆኑ በቀጣይ የህትመት ሥራው በጀት ተይዞለት ተግባራዊ እስከሚደረግ ድረስ በዝዋይ እና በሸዋሮቢት ማረሚያ ማዕከላት በቅጾቹ ላይ የማረሚያ ማዕከሉን ክብ ማህተብ በማሳረፍ እንዲጠቀሙ በሚል ታሳቢ ሥራው እየተሠራ መሆኑን እና ሆኖም ግን በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያ ቤት ያለው የእርሻ መሬት ከሠርቶ ማሳያ ያለፈ ባለመሆኑ ቅጾችን የመጠቀም ክፍተት መስተዋሉን እና እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ የሰጠው አስተያየት ትክክል ስለሆነ በቀጣይ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አሰተያየት ሰጥተዋል፡፡

84. በመሆኑም በምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾችን ባለመጠቀማቸው ከምርት አሠባሠብ፣ አቀራረብ እና አሻሻጥ ድረስ ያሉ ተግባራት ወጥ በሆነ አሰራር እንዳይሰራና ለቁጥጥር አመቺ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

ሁሉም ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቶች አስተዳዳሪ ሪፖርት ማቅረባቸውን በተመለከተ፣

85. የምርት ዋጋ ተማኝ፣ የምርት አስረካቢ እና የምርት አስወጋጅ ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ በናሙና በተመረጡ ማዕከላት በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት እንደማያቀርቡ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

87. ስለጉዳዩ በናሙና በተመረጡ የዝዋይ፣ የሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከላት እንዲሁም የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከላት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ኮሚቴዎች አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቶቹ አስተዳዳሪዎች ሪፖርት እንደማያቀርቡ እና ለዚህም ምክንያት በቃለ ጉባኤ ያልተደገፈ የቃል ውይይት ስለሚያደርጉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

88. ይሁን እንጂ፣ የአስተዳደሩ የግብርና ምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብ እና አሻሻጥ መመሪያ ሁሉም ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ የማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለባቸው የኮሚቴዎች የስብሰባ ሥርዓት አንቀጽ 23 ላይ በግልጽ የተቀመጠ ስለሆነ፣ መመሪያውን አለመከተላቸውን ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

89. የምርት ዋጋ ተማኝ፣ የምርት አስረካቢ እና የምርት አስወጋጅ ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ የማረሚያ ቤቶቹ አስተዳዳሪ ሪፖርት ባለማቅረባቸው የተከናወኑ ስራዎች በማዕከላቱ በሪፖርት መልክ እንዳይቀመጡና ለመረጃ ፈላጊ አካል ግብአት እንዳይሆኑ እና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን የተሟላ እንዳይሆን አድርጓል፡

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የስርዐተ-ፆታ እና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጉዳይ በስራ እቅዱ ተካቶ (Mainstreaming) በሁሉም የስራ ሂደት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

90. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የስርዐተ-ፆታ እና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጉዳይ በስራ እቅዱ ተካቶ (Mainstreaming) በሁሉም የስራ ሂደቶች ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

91. በናሙና በተመረጡ ማዕከላት በዝዋይ፣ በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል እንዲሁም በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል በስራ ዕቅዳቸው ላይ የስርዐተ-ፆታ እና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጉዳይ በስራ እቅዳቸው ላይ ተካቷል፡፡
92. እንዲሁም ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምርመራ ስራ በተሳካ ሁኔታ እንደሚሰሩ በናሙና የተመረጡ ማዕከላት የዝዋይ፣ የሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል እንዲሁም የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል የበሽታ መከላከል እና የጤና አገልግሎት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡
93. ይሁን እንጂ በናሙና የተመረጠው የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምርመራ ስራ በተሳካ ሁኔታ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው የቢሮ ጉብኝት ወቅት ምክር ሰጪዋ (ካውንስለር) እና የጥሬ መረጃ ጭኑት (ዳታ ክለርክ) ሰራተኛዋ በአንድ ቢሮ ተደራቢ ሁነው እንዲሠሩ መደረጉን እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምክር እና ምርመራ ለማከናወን የሚያስፈልገው ፕሮቶኮል በቢሮ አለመኖር ለማወቅ ተችሏል፡፡
94. እንደዚሁም በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል የበሽታ መከላከል እና የጤና አገልግሎት ሪፖርት ለኦዲቱ ቀርቦ ሲታይ፡- የታህሳስ ወር 2005 ወርሃዊ ሪፖርት ላይ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ ቅድመ ትምህርት የተሰጣቸው አገልግሎቱን ያገኙ ታራሚዎች ብዛት ሴት 11 ወንድ 1630 በማለት ሪፖርት የተደረገ ሲሆን፣ ነገር ግን በማዕከሉ ሴት ታራሚዎች የሌሉ መሆናቸው በኦዲቱ የተረጋገጠ በመሆኑ ሪፖርቱን ለማመን አልተቻለም፡፡
95. ከላይ ለቀረቡት ሁኔታዎች የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊ፣ በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያ ቤት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምርመራ ክፍል የዳታ ክለርክ ባለሙያ እና ምክር ሰጪ (ካውንስለር) በአንድ ክፍል መቀመጣቸው አግባብ አለመሆኑ በወቅቱ የተሰጠው ጥቆማ አግባብነት ያለው እንደሆነ እና ሆኖም የዳታ ክለርክ ባለሙያውም በሳምንት አንድ ቀን ብቻ በክፍሉ በመገኘት ስራውን ስለሚያከናውን እና የድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ካለበት የክፍል እጥረት አንጻር ይህ ሊደረግ መቻሉንና በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ ቅድመ ትምህርት የተሰጣቸው አገልግሎቱን ያገኙ "የሴት ታራሚ ቁጥር" ተብሎ የተገለጸው ስህተት

መሆኑን እና በማዕከሉ ሴት ታራሚዎች አለመኖራቸውን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ላይ አሰተያየታቸውን ሰጥተዋል፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያ ሃሳቦች

96. **ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች ሲታዩ፡-**

- ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ ምርቶችን አያያዝና መጋዘን አቀማመጥ ሁኔታ አጥጋቢ አለመሆኑ፤
- ምርት ጊዜና ወቅት ጠብቆ አለመሰብሰብ እና የሚፈለገውን ገቢ ማግኘት አለመቻሉ፤
- በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል የደረሱ ምርቶችን ማዕከሉ ለሽያጭ ማዋል አለመቻል፤
- የዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል የምርት ማቆያ መጋዘን አለመኖሩ፤
- በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ በመጋዘኑ ከሶስት አመት በፊት ጊዜው ያለፈበት አደገኛ ኬሚካል ከተለያዩ ከመአከሉ ምርቶች (ቲማቲም፣ ማንጎ፣ በቆሎ.....ከመሳሰሉት) ጋር መቀመጡ፤
- በማዕከላት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያሳትመው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቢኖርም ምርቱ በችርቻሮ በሚሸጥበት ጊዜ ለገዢ ለገዙት ንብረት ሕጋዊ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ አለመቆረጡ፤
- በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ ታክስ የሚል ሳይኖር የከፈለበት ምክንያት ቦታ አጠገብ ላይ በእስክቢርቶ "ታክስ" የሚል ማስገባታቸውና የምርቱ ዋጋ ላይ 5% ማሰባቸውን እና ለዚህም ታክስ ምንነት ምክንያት ማቅረብ አለመቻላቸው ተገቢ አለመሆኑ፤
- በዝዋይ እና በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል በምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ አለመደረጉ፤
- ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት ፣ ደረጃ ፣ መጠን ፣ የአቅርቦት እለትና ሰዓት ፣ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ የሚጠቀሙበት አሰራር አለመኖሩ፤

- ለደንበኞች ምርቱን ለመሸጥ የማስተዋወቅ ስራ አለመሰራታቸው፤
- የማዕከላት የምርት አሻሻጥ፣ ተግባራትና ዘዴዎቹ ግልጽ አለመሆናቸው፤
- ማዕከሎች ምርታቸውን የሚያሳዩበት የቦታ ጥበት መኖሩ እና ምርትን ለማሳየት የሚያስችል ሱቅ አለመሆናቸው፤
- የሚሸጡ ምርቶች ማስተዋወቂያ ዘዴዎች አጥጋቢ አለመሆኑ፤
- የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለግብርና ምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ ተፈጻሚነቱ በአስተዳደሩ ስር ለሚገኙ ለዝዋይ፣ ለድሬዳዋ እና ለሸዋሮቢት ማረሚያ ቤቶች እንዲውል መመሪያ ቢያወጣም ተግባራዊ ለመደረጉ ክትትል አለመደረጉ፤
- የኢንዱስትሪ ምርቶች አሻሻጥ መመሪያ አለመዘጋጀቱ፤
- የምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብ እና አሻሻጥ መመሪያ ቢኖርም እስከታች ወርዶ የሚሰራበት አለመሆኑ እና የኮሚቴዎች አባላትም እንዲያውቁት አለመደረጉ፤
- በማዕከላት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ በኦዲትና ኢንስፔክሽን ጽ/ቤት ኦዲት ተደርጎ አለማወቁ፤
- በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል የንብረት ክፍል በንብረት ገቢና ወጪ መዝገብ በአንድ ሰው መሠራቱ፤
- በናሙና በተመረጡ በዝዋይ እና በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል በምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾችን አለመጠቀማቸው፤
- የዋጋ ተመን ጥናት መረጃ ማሰባሰቢያ እና በርክክብ ወቅት የምርት መጠንን የሚገልጽ መረጃዎች በነጭ ወረቀት መጠቀማቸው፤
- በማዕከላት ሁሉም ኮሚቴዎች በመመሪያው መሠረት በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለየማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት አለማቅረባቸው፤
- የተከናወኑ ስራዎች በማዕከላቱ በሪፖርት መልክ አለመቀመጣቸው፤
- የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምርመራ ክፍሉ አመቺ አለመሆኑና፤

ምክር ሰጪዋ (ካውንስለር) እና የጥሬ መረጃ ጭነት (ዳታ ክለርክ) ሰራተኛዋ በአንድ ቢሮ መቀመጣቸው አግባብ አለመሆኑ፤

- በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምክር እና ምርመራ ለማከናወን የሚያስፈልገው ፕሮቶኮል በቢሮ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

ባጠቃላይ በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት ያሉ ተግባራት ወጥ በሆነ አሰራር የመስራት ሁኔታ እንደሌለና ለቁጥጥር አመቺ በሆነ የአሰራር ስራ በተጠናከረ መልክ ባለመኖሩ የውስጥ ገቢው በተሟላ ሁኔታ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

97. ስለሆነም ከላይ የተገለጹትን የአሰራር ግድፈቶች ለማስወገድ ወይም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

98. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ ምርቶችን አያያዝና በመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታ በቅድሚያ ሊያውቅ የሚችልበትን አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡
99. የማዕከላቶች ምርት በማሳ ላይ ሆነው ከመበላሸታቸው በፊት ወቅትና ጊዜያቸውን ጠብቀው ሊነሱ ይገባል፡፡
100. ምርት አቅራቢው ምርት ለማዕከላት ለሽያጭ ክፍል ሰራተኞች ከማቅረቡ በፊት ሱቁ ውስጥ ምን ያህል የምርት መጠን መኖሩን ማወቅ ይገባዋል፡፡
101. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ ምርቶች አያያዝ እና በመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታ የመንግስትን የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መርሆዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
102. በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ በመጋዘኑ የሚገኘውና ከሶስት አመት በፊት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት አደገኛ ኬሚካል (Bayleton 25 WP) በፍጥነት ሊወገድ ይገባል፡፡
103. የማረሚያ ቤቱ ምርቱ በሚሸጥበት ጊዜ ለገዢ ለገዙት ንብረት ሕጋዊ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሊሰጥ ይገባል፡፡
104. በማዕከላት በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ ታክስ የሚሰበሰብ ከሆነና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያዘጋጀው የገቢ ደረሰኝ ሥራ ላይ የማይቻል ከሆነ አስፈቅዶ በግልጽ የታተመ የታክሱ ዓይነት እና መጠኑ በተቀመጠ ደረሰኝ መጠቀም ይገባል፡፡
105. በማዕከላት በምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡
106. ምርት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት ፤ ደረጃ ፤ መጠን ፤ የአቅርቦት እለትና ሰዓት ፤ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ አሰራር በሁሉም ማዕከላት ወጥ በሆነ መንገድ ሊተገበር ይገባል፡፡
107. የቲማቲም እና የሽንኩርት ምርት በርክክብ ወቅት ያለው የክብደት መጠንና፤ መሸጫ ሱቅ በሚገባበት ጊዜ ያለው የክብደት መጠን መለያየቱና ቲማቲሙ እና ሽንኩርቱ

በፍሰት እና ሲያድር ሊያመጣ የሚችለውን የሚዛን ጉድለት ግንዛቤ ተወስዶ ሊወሰን ይገባል፡፡

108. አስተዳደሩ ምርቱን ለመሸጥ በውስጥ ማስታወቂያ፤ በብዙሃን መገናኛ ቴሌቪዥን፤ ሬዲዮ፤ ጋዜጣ፤ በመ/ቤቱ ድረ-ገጽና በአውደ ራዕይ (በመረጠው) ሊያስተዋውቅ ይገባል።
109. የምርት አሻሻጥ፤ ተግባራትና ዘዴዎቹ ግልጽ ሊሆኑ ይገባል፡፡
110. ማዕከሎች ምርታቸውን የሚያሳዩበት ቦታ እና የምርት ማቆያ መጋዘን እንዲኖራቸው ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡
111. አስተዳደሩ የግብርና ምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ መመሪያን የተፈጻሚነቱ ወሰን ለሚያርፍባቸው አካላት መድረሱንና በትክክል መተግበሩን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡
112. የኢንዱስትሪ ምርቶች አሻሻጥ መመሪያ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
113. በገቢ አሰባሰብ ለውስጥ ኦዲት ስልጠና ሊሰጥና በውስጥ ኦዲት ከምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ እንዲሁም የውስጥ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ በውስጥ ኦዲት፤ ኦዲት ሊያስደርግ ይገባል፡፡
114. በማዕከላት ከምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ እንዲሁም የውስጥ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ በኦዲትና ኢንስፔክሽን ጽ/ቤት፤ ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡
115. የፌዴራል የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል የውስጥ ኦዲት ሠራተኛ ሊመደብ ይገባል፡፡
116. የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል የንብረት ክፍል ከስራ ክፍፍል ስርአት (Segregation of duties) አንጻር ተጨማሪ ሰው ሊመድብ ይገባል፡፡
117. በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጻ ቅጾች ለማዕከላት ኮሚቴዎች በማሳወቅ እና ግንዛቤ በመፍጠር እንዲጠቀሙበት ሊደረግ ይገባል፡፡
118. ሁሉም የማዕከላት ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለየማረሚያ ቤቶቹ አስተዳዳሪ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡
119. በማዕከላት የምርቶችን የብልሽታቸዉን መንስኤ ከምርት አቅራቢው እስከ ተረካቢው ድረስ ያለው ተጠያቂነትን የሚያጠናክር ክትትል መደረግ አለበት፡፡
120. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለተደራጁም ሆነ በመደራጀት ላይ ለሚገኙት ታራሚ ማህበራት ህጋዊ ዕውቅና እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
121. የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምርመራ ክፍሉን አመቺ ለማድረግ የምክር ሰጪዋ (ካውንስለር)

እና የጥሬ መረጃ ጭነት (ዳታ ከለርክ) ሰራተኛዋ ቢሮ ለየብቻ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡

122. ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ ቅድመ ትምህርት የተሰጣቸውን ታራሚዎች በሪፖርት ሲቀርብ ትክክለኛነቱን መረጋገጥ አለበት፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለስራችን መቃናት ሙሉ ትብብር ላደረጉልን ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊዎችና ሠራተኞች፤ በናሙና ለተመረጡ ማዕከላት ኃላፊዎችና ሰራተኞች እንዲሁም ታራሚዎች መረጃ በመስጠት ላደረጉልን የሥራ ትብብር ሁሉ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

<u>**አባሪ 1**</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

<u>በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ ክትትልና አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ የተዘጋጁ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/</u>

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ፦ <u>የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር</u>

የኦዲት ጭብጦች (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርት (Evaluative Criteria)
1. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ ስርአት በመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያዎችና ደንቦች የሚከናወን ስለመሆኑ ማጣራት፣	1. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ከውስጥ ገቢ የመንግስትን ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ በሕግ የተፈቀደለት መሆን ይገባዋል፡፡
	2. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ማናቸውም የመንግስት የውስጥ ገንዘብ ሲሰበስብ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡
	3. በማዕከላት በምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ መደረግ አለበት፡፡
	4. የምርት ማቅረቢያ ማዘዣ ምርት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት ፣ ደረጃ ፣ መጠን ፣ የአቅርቦት እለትና ሰዓት ፣ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ ማዕከላት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡
	5. የማዕከላት አምራቾች የሚሸጡትን ምርቶች አይነትና የሽያጭ ፕሮግራም ለደንበኞች በግልጽ በሚታይ ቦታ ማስታወቂያ መለጠፍና እንደአስፈላጊነቱ በሚዲያ ሊያስነግሩ ይገባል፡፡

	6. የገበያው ሁኔታ በአከባቢው ካለው የገበያ መረጃ አንጻር ለሽያጭ በቀረቡ ምርቶች የዋጋ ተመን ላይ አሉታዊ ወይም አወንታዊ ተጽዕኖ ሲፈጥር በድጋሚ የዋጋ ማሻሻያ ተመን እንዲዘጋጅ ከአምራቹ ወገን በገበያ ምርት ባለሙያው መሰረት ለሚመለከተው ክፍል ሊቀርብ ይገባል፡፡
	7. የግብርና ምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ ላይ ማዕከላቶች የምርት ተማኝ፤ የምርት አረካካቢ እና የተበላሹ የግብርና ምርቶች አስወጋጅ በማረሚያ ቤቱ አስተዳደር የተሰየሙ ኮሚቴዎች ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	8. በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾች፡- የዋጋ ተመን የሚወጣላቸው ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 001፤ የዋጋ ተመን ጥናት መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽና ቃለ ጉባኤ ቅጽ 002፤ ለሽያጭ የሚቀርቡ ምርቶች መጠየቂያ ቅጽ 003፤ የተተመኑ ምርቶች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረጊያ ቅጽ 004፤ የዋጋ ማሻሻያ ተመን የተጠየቀባቸው የምርት ዓይነቶች ማሳወቂያ ቅጽ 005፤ በዋጋ ማሻሻያ ተመን ምክንያት ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ የሆኑ ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 006፤ የተበላሹ ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 007 እና የተበላሹ ምርቶች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ማሳወቂያ ቃለ ጉባኤ ቅጽ 008 የማረሚያ ቤት አምራቾች ቅጹን ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡
2. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ ስርአት ላይ ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ሥራ የሚያከናውን ስለመሆኑ ማጣራት፤	9. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የተጠናከረና ወጥ የሆነ የመስክ ጉብኝት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	10. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ መመሪያ ሊያዘጋጅና ለሚመለከታቸው ሊያሰራጭ ይገባል፡፡
	11. ሁሉም ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡
	12. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ ምርቶችን እያያዘና በመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታ በቅድሚያ ሊያውቅ ይገባል፡፡
	13. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ በውስጥ ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡

	14. በምርት አሰባሰብ፣ አቀራረብና አሻሻጥ ላይ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
	15. የኮሚቴውን የውሳኔ መፈራረሚያ ቅጾችንና የፋይናንስን ሞዴላ ሞዴሎችን በአግባቡ መያዛቸውን፣ ርክክብ የተፈጸመባቸውንና ሽያጭ የተከናወነባቸውን ምርቶች ገቢ በትክክል ለመንግስት ፈሰስ መደረጉን የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
	16. በገቢ አሰባሰብ የተከናወኑ ሥራዎችና ያጋጠሙ ችግሮች የሚገመገሙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡
	17. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለገቢ አሰባሰብ ስርአት በፍላጎት ጥናት ላይ የተመሠረተ ሥልጠና ለሠራተኞቹ ሊሰጥ ይገባል፡፡
	18. በማዕከላት ለልማት ስራ ለተደራጁም ሆነ በመደራጀት ላይ ለሚገኙት ታራሚዎች የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
3. በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ ስርአት ላይ ተገቢው የመረጃ አያያዝ ስለመኖሩ ማጣራት፣	19. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የራሱን በጀት አስተዳደር በመምራት የተፈቀደለትን ገቢ በመሰብሰብና በመመዝገብ ከዚያም ሪፖርት በማድረግ የተጠናከረ ተጠያቂነት ሊኖረው ይገባል፡
	20. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የስርዐተ-ፆታ እና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጉዳይ በስራ እቅዱ ተካቶ (Mainstreaming) በሁሉም የስራ ሂደት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

አባሪ 2

<u>የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር አደረጃጀት</u>